# ጋሽ አበራ ሞላ የት ደረሰ ?

**ጋሽ አበራ ሞላ**
**ጋሽ አበራ ሞላ**
**አበደ ይሉታል ዓላማዉ ሳይሞላ?**

ዉስጠ አዋቂ ኢትዮጲያዊ
Feb 22, 2009

ታዋቂ አርቲስት ተብለዉ ከሚቆጠሩት መስመር ባይሰለፍም ታ ታሪ ከሚባሉት አማ ተር አርቲስቶች ዉስጥ እንደነበር አዉቃለሁ፡፡ ጋሽ አበራ ሞላ ሌሎች ዘመናዊ ፖለቲከኞች የበረሃ ስም እንዳላቸዉ ሁሉ የሱ የሽሮ ሜዳ ስሙ ነዉ፡፡ አዲስ አበባ ከተማ በስፋት የሚታወቀዉ በዚሁ ቅጽል ስሙ እንጂ በእዉነተኛ ስሙ አልነበረም፡፡ የጋሽ አበራ ሞላ እዉነተኛ ስሙ አርቲስት ስለሺ ነዉ፡፡ ጋሽ አበራ ሞላ እንደማንኛዉም ኢትዮጲያዊ በዚህም በዛም ብሎ አሜሪካን አገር ከመጣ በኋላ በሁለገብነት (ትምህርት፣ ሥራ፣ ወዘተ ሲል) ሳይታወቅ ሃያ ምናምን ዓመታት ካሣለፈ በኋላ ጊዜዉንና ሁኔታዉን ጠብቆ እንደ አንዳንድ ኢትዮጲያዊ የማንነት ጥያቄ (identity crises) በማንሳት አገሩ ለመግባት ወሰነ፡፡ የገባበት ሰዓት ደርግ ፈረሰ፣ የቀዝቃዛዉ ጦርነት አበቃ፡፡ ወያኔ የተባለ ዴሞክራት ተብዬ ከጫካ ተነስቶ ወደ አገሩ ይገባል በሚል ንድፈ-ሃሳብ ወደ አገሩ ገባ፡፡ በሚገባበት ግዜ አልጠራጠርም ጥቂት የጥንት ወዳጆቹን አማክሮ እንደገባ አዉቃለሁ፡፡

ጋሽ አበራ ሞላ እንደሌሎቹ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የካፒታል ኢንቬስትመንት (investement) ይዞ አልገባም ፡፡ እርሱ ለራሱ ያጠራቀመዉ ቅርስ አልነበረዉም፡፡ ሃብቱም ንብረቱም፣ ከሙዚቃ ክሮቹ ጋር የተያያዘችና ግፋ ቢል ያሳተማቸዉ ጥቂት ነገሮች ነበሩ፡፡ ይህም ቅርስ እንኳን አዲስ አበባ በሕይወት ሊያኖር ቀርቶ፣ አሜሪካን አገርም ሊያኖረዉ አይችልም፡፡ ስለዚህም ጋሽ አበራ ሞላ የሚል የበጎ አድራጎት ድርጅት (NGO) ያቋቁማል፡፡ የፖለቲካ ፕሮጀክት ይዘዉ ተልኮአቸዉን ለሚሟላት ከሚንቀሳቀሱ ከ1500 በላይ ካሉት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ዉስጥ አንዱ በመሆን እየሰራ ነበር፡፡ የጋሽ አበራ ሞላ ድርጅት የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችን በማሰባሰብ ከተማችንን እናፅዳ በሚል መርህ ወጣቱ ትዉልድ በወያኔ ስርዓት ላይ እንዳያተኩርና እንዳያምፅ ለማድረግ የተዘጋጀ የዉስጥ ዓላማ የነበረዉ የበጎ አድራጎት ድርጅት ነበር፡፡

ወያኔ ከዓለም ገንዘብ አበዳሪ ድርጅቶች (IMF, ect.) ጋር በመስማማት ባወጣወ ፀረ-ኢትዮጲያ የኢኮኖሚ ተሃድሶ ፕሮግራም ፣ ሕዝብ በፖሊሲዉ ምክንያት ተቆጥቶ እንዳያምጽ ለማድረግ ሕዝባዊነት ያላቸዉ ን የሞያ ማህበራት አፈራረሰና በቦታቸዉ ሲቪክ ህብረተሰብ በሚል ስያሜ በመስጠት እነዚህን የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በቦታዉ ተካቸዉ ፡፡ ይህንን እኩይ ተግባራቸዉን ሥራ ላይ ሲያዉሉ የመጀመሪያ ሰለባ ያደረጋቸዉ የኢትዮጲያ ሠራተኞች ማህበርን፣ የኢትዮጲያ መምህራን

ማህበርና የባንክ ሰራተኛ ማህበርን ነበር፡፡ በነዚህ ማህበራት ዉስጥ የነበሩ መሪዎች ተገድለዋል፣ ታስረዋል የተቀሩትም ከአገር ተሰደዉ ወጥተዉ በተለያየ፣ አገሮች ዉስጥ በስደት ይኖራሉ፡፡

በአንፃሩም ህዝብ እንዳይደራጅ በመንደር (በጎሳ) እንዲከፋፈል በማድረግ የህዝብን ሃይል ሲያዳክሙ ቆይተዋል፡፡ በተለይም ለህዝብ የተለያየና የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ወደ አንድ ዓላማ እንዳይመጣ በጥልቀት ሲንቀሳቀሱ ቆይተዉ የወያኔን እድሜ ሊያራዝሙ በቅተዋል፡፡ ዛሬ ወያኔ እነዚህ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በደርግ ላይ የፈጸሙትን አድራጎት በራሱ ላይ ይጠቀማሉ ብሎ ስለገመተ (የጥቅም ግጭት) የፖሊሲ ለዉጥ ለማምጣት ተገዷል፡፡

በተለይም የፖለቲካ ፕሮጀክቶች ይዘዉ ከሚንቀሳቀሱት መሃከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፡ ወያኔን ከጫካ ድረስ ተደራድረዉ ካስገቡት ከኢንተር አፍሪካ ግሩፕ፣ ህገ መንግስት አርቅቀዉ አንቀጽ 39 ያጸደቁት የኢስት አፍሪካ ሰላምና ዴሞ ክራሲ በጎ አድራጎት እንዲሁም የኢትዮጲያ ሴቶች ጠበቆች ማህበርና፣ የኢትዮጲያ ኢኮኖሚ ክ ኢንስቲቲዉትን ጨምሮ በቀጥታ በባዕድ መንግስት እንዲሰሩ የህዝብ ወገን በመምሰል ሲያጠፉት ኖረዉ የህዝብ ትግል መና እንዲሆን አድርገዋል፡፡

በዉጪ የሚገኙ የሞያ ማህበራት መሪዎች ጉዳዩን ከኔ ይበልጥ በጥልቀት የተሰራዉን ሻጥር ስለሚያውቁ በስፋት ለህዝብ ቢያስረዱ መልካም ይመስለኛል፡፡

ወደ ተነሳሁበት መለስ ልበልና፣ ጋሽ አበራ ሞላ አላበደም፤ ምናልባትም መ ንገዱን እደሳተ ባቡር አንድ ቦታ ቆሞ ይገኛል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ያጋጠማቸዉ ጥቂቶች አይደሉም ፣ ቤተ መንግስትና ጫት ቤት ይቁጠራቸዉ እላለሁ።